# 181st Semiannual General Conference
# Saturday Priesthood Session, October 1, 2011

ሁላችንም ተመዝግበናል

በሽማግሌ ጀፍሪ አር ሆላንድ

የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን አባል

ወንድሞች፣ በወንድምነት መንፈስ፣ በዚህ ምሽት በግልፅነት ላነጋግራችሁ እፈልጋለሁ። በዚህም ግልፅነት የአሮናዊ የክህነት ባለስልጣን ወጣት ወንዶችንም እጨምራለሁ።

የጆሴፍ ስሚዝን የመጀመሪያ ራዕይ ታላቅነት ስንናገረት፣ ይህ ከመምጣቱ በፊት የሚቻል ከሆነ ልጁን ለማጥፋት ነገር ግን በማንኛውም ይመጣ የነበረውን ራዕይ ለመገደብ ስለጣረው የሚያስፈራ መጋፈጥን በደንብ አንመለከትም። ስለአጥፊው መናገር ካለብን በላይ አንናገርም፣ እናም ስለእርሱ መናገርን በፍጹም አልወድም፣ ነገር ግን የወጣቱ ጆሴፍ አጋጣሚ እያንዳንዱ ሰው፣ እንዲሁም እያንዳንዱ ወጣቶች፣ ማስታወስ ያለበትን እንዲያስታውን ያደርገናል።

መጀመሪያ፣ ሰይጣን ወይም ሉሲፈር ወይም የሀሰት አባት እውነት፣ የክፉነት ህያውነት ነው። በሁሉም ሁኔታ መንቀሳቀሻው ተንኮል ነው። ሁለተኛ፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ የኢየሱስ ክርስቶስን የኃጢያት ክፍያ፣ እናም የሰላምና የደህንነትን ስራ ለዘለአለም ይቃወማል። የትም ይሁን መቼ ከእነዚህ ነገሮች ጋር ይጣላል። እንደሚሸነፍና በመጨረሻው እንደሚጣል ያውቃል፣ ነገር ግን ከእርሱ ጋር የሚችለውን ያህል ይዞ ለመሄድ ውሳኔ አለው።

የዘለአለም ህይወትን ለማግኘት በሚፎካከርበት ዲያብሎስ የሚጠቀማቸው ዘዴዎች ምንድን ናቸው? እንደገናም የቅዱስ ጥሻ አጋጣሚ የሚያስተምር ነው። ወደፊት የሚመጡትን ለመቃወም በመጣር ሉሲፈር “በእኔ ላይ የሚያስገርም ተፅዕኖ ኖሮት እንዳልናገርም አንደበቴን አሰረው” ብሎ ጆሴፍ ጽፎ ነበር።

ሰይጣን በቀጥታ ለመግደል አይችልም። ይህም ማድረግ ከማይችላቸው ነገሮች አንዱ ነው። ነገር ግን ስራውን ለማቆም የሚጥርበት አንደበትን በማሰር ውጤታማ ለማድረግ ይችላል። ወንድሞች፣ ይህ ሁኔታው ከሆነ፣ በዚህ ምሽት በጥሩ እና መጥፎ መካከል ስላለው ጦርነት የሚያስቡ ተነስተው የሚናገሩ ወጣት እና ጎልማሳ ሰዎች እፈልጋለሁ። በጦርነት ላይ ነው ያለነው፣ እናም ለሚቀጥሉት ትንሽ ደቂቃዎች፣ የሚለመልም አንድ ሰው ለመሆን እፈልጋለሁ።

“ሁላችንም ተመዝግበናል” የሚለውን መዝሙር መዘመር አለብኝ? “ለወታደሮች እየጠበቅን ነን፤ ማን ፈቃደኛ ይሆናል?” የሚለውን ግጥም ታውቃላችሁ። እንዲታጠቁ ፈቃደኛ እንዲሆኑ የምንጠይቃቸው ጥይት መተኮስ ወይም ቦምብ መወርወር አያስፈልጋቸው። አይደለም፣ የምንፈልጋቸው ወታደሮች “ከእግዚአብሔር አፍ የሚመጡትን ቃላት ሁሉ” እንደ መሳሪያ የሚጠቀሙትን ነው። ስለዚህ በዚህ ምሽት የምፈልጋቸው ምላሳቸውን በፈቃደኛነት እንዲታሰሩ የማይፈቅዱ ነገር ግን በጌታ መንፈስ እና በክህነት ስልጣናቸው ሀይል አፋቸውን የሚከፍቱ እና ታዕምራትን የሚናገሩ የወንጌል መልእክተኞችን ነው። የድሮ ወንድሞች እንዳሉት፣ እንደዚህ አይነት ንግግር የእምነት “ታላቅ ስራ የተሰራበትና የሚሰራበት” መንገድ ነው ብለዋል።

የአሮናዊ የክህነት ባለስልጣኖቹ ወጣቶች እንዲነቁና እንዲያዳምጡ እጠይቃቸዋለሁ። ለእናንተ ስለአትሌት ምሳሌ ልስጣችሁ። እናንተንና ስራውን ከሚጠላ ጋር ነው

የምንፎካከረው፣ ስለዚህ አሰልጣኝ ፉክክሩ ቅርብ ሲሆን እና ማሸነፍ ሁሉም ነገር በሚሆንበት ጊዜ አትሌቶችን እንደሚያነጋግረው አነጋግራችኋለሁ። በጨዋታው ጊዜ ይህ አሰልጣኝ የሚነግራችሁ ቢኖር ይህን ለመጫወት አሁን ከሆናችሁበት በላይ በምግባረ ጥሩነት ንጹህ እንድትሆኑ ነው። በመልካም እና ክፉ መካከል ባለው የእውነት ህይወት ጦርነት ፣ ፈተና በሚመጣበት ጊዜ ሁሉ ለጠላት ለመጫወት፣ ከእዚያም ምንም ሳይኖር በቤተመቅደስና በሚስዮን ጊዜ ለአዳኝ ቡድን ተጫዋች ለመሆን ለመዘጋጀት አትችሉም። ወጣት ጓደኞቼ ያን ማድረግ አትችሉም። እግዚአብሔር ሊሳለቅበት አይችልም።

እኔና እናንተ የተለያዩ ምርጫዎች አሉን ። ለሚስዮን አገልግሎት ብቁ ለመሆን የሚችሉ ብዙ ሺህ የአሮናዊ የክህነት ባለስልጣን የሆኑ ወጣት ሰዎች በቤተክርስቲያኗ መዝገብ ላይ ይገኛሉ። ነገር ግን ጉዳዩ እነዚህ ዲያቆኖች፣ መምህራን፣ እና ካህናት ሽማግሌዎች ለመሆን እንዲሾሙና በሚስዮን እንዲያገለግሉ በብቁ ተሳታፊ እና ብቁ እንዲሆኑ ማድረጉ ነው። በቡድኑ አባል የሆኑት ወጣቶች በቡድኑ እንዲቆዩና በልባቸው በሙሉ መጫወት ሲገባቸው በደንብ አለምጫወትን እንዲያቆሙ እንፈልጋለን ። በአትሌት ፉክክሮች ሁሉ፣ ለመፎካከር በውስጡ መቆየት ያለባቸው መስመር አለ፣ እናም በእዚህ ስራ ከእርሱ ጋር እንዲያገለግሉ የተጠሩት መተላለፍ የማይችሉት የብቁነትን መስመር ስኋል። ማንኛውም የወንጌል መልእክተኛ ለወሲብ ሀጥያት፣ ለስድብ፣ እና ወሲባዊ ነገሮችን የሚያሳዩትን ለመመልከት ንስሀ ሳይገቡ ሌሎች ለእነዚህ ነገሮች ንስሀ እንዲገቡ ለመጠየቅ መጠበቅ አይችልም። መንፈስ ከእናንተ ጋር አይገኝም እናም እነዚህን ቃላቶች ለመናገርም አትችሉም። እናንተ ሌሂ “የተከለከለ መንገድ” ብሎ በጠራው ለመጓዝ እናም ሌሎችን “በጠባብና ቀጥተኛ” መንገድ ለመምራት ለመጠበቅ አትችሉም---ይህም ሊደረግ አይቻልምና ።

ነገር ግን ለዚህ ፈተና ለእናንተም ሆነ ለምትሄዱላቸው መርማሪዎች መልስ አለ ። ማንም ብትሆኑ እናም ምንም ብታደርጉ፣ ምህረት ለማግኘት ትችላላችሁ። ማንኛችሁም ወጣቶች የምትታገሉበትን መተላለፊያ ከኋላችሁ ለመተውትችላላችሁ። ይህም “የምህረት ታዕምራት፣ ” የኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ ታዕምራት ነው። ነገር ግን ለወንጌሉ በልብ ተሣታፊ ሳትሆኑ ይህን ለማከናወን አትችሉም፣ እናም በሚያስፈልግበትም ንስሀ ያለመግባት ልታደርጉትም አትችሉም። እናንተ ወጣቶች ተሳታፊና ንጹህ እንድትሆኑ ነው የምጠይቃችሁ። ።

ወንድሞች፣ በግልፅ የምንናገራችሁ በዘዴ የሚነገረው በብዙም ጊዜ አይሰራም። በግልፅ የምንናገረው ሰይጣን እናንተን ለማጥፋት ውሳኔ ያለው እውነተኛ ፍጥረት ስለሆነ ነው። እናም በእድሜ ወጣት የሆኑት ተጽዕኖው ይሰማቸዋል። ስለዚህ በሽሚዛችሁ ይዘናችሁ በምናውቀው ያህል እንጮህባችኋለን ።

አዳምጡ! የጦርነት ድምፅ በግልፅ ይሰማል፤
ኑ በሰልፉ ተሳተፉ! ኑ በሰልፉ ተሳተፉ!

ውድ ወጣት ጓደኞቼ፣ ብዙ አስር ሺህ የሚሆኑ የወንጌል መልእክተኞች በሚመጡት ወራትና አመታት ያስፈልገናል። ከተሾሙ፣ ተሳታፊ፣ ንጹህ፣ እና ለማገልገል ብቁ ከሆኑ ከአሮናዊ የክን=ህነት ባለስልጣናት እነዚህ መምጣት አለባቸው።

ላገለገላችሁት እናም እያገለጋላችሁ ላላችሁት፣ ላደረጋችሁት መልካም ነገሮች፣ እናም ለነካችኋቸው ህይወቶች፣ እናምም ለባረካችኋቸው ቤተሰቦች እናመሰግናችኋለን ። ተባረኩ! በጤንነት ወይም እነርሱ ሊቆጣጠሩት በማይችሉት ጉዳይ ለማገልገ የማይችሉ እንዳሉ እናውቃለን ። ስለፍላጎታችሁ እናውቃለን እናም ታማኝነታችሁን እናከብራለን ። የእኛን ድንቀትና ፍቅር አላችሁ። እናንተ በቡድናችን ናችሁ እና ከሙሉ ጊዜ አገልግሎት

በምትለቀቁበትም ጊዜ ሁልጊዜም በቡድናችን ትሆናላችሁ። ነገር ግን ሌሎቻችሁን እንፈልጋችኋለን።

አሁን፣ የመልከ ጸዴቅ የክህነት ባለስልጣን ለሆናችሁት። ፈገግ ብላችሁ በሚመቸው ሶፋ ላይ አትቀመጡ። ገና አልጨረስኩም። በቤተክርስቲያኗ በሚስዮን የሚያገለግሉ ብዙ ሺህ ባልና ሚስቶች እንፈልጋለን። የሚስዮን ፕሬዘደንቶች በሙሉ እነርሱን ለማግኘት ይለምናሉ። በሚያገለግሉበት በሙሉ፣ አስራ ዘጠኝ አመት የሆናቸው ወጣቶች ሊያመጡት የማይችሉትን ባልና ሚስት ሚስዮኖች ጎልማሳነትን በስራው ያመጣሉ።

ተጨማሪ ባልና ሚስት በሚስዮን እንዲያገለገሉ ለማበረታታት፣ ቀዳሚአመራር እና አስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ባለፉት 50 አመታት በሚስዮን ስራ ታይተውየማይታወቁ ልዩ ነገሮች አድርገዋል። በዚህ አመት ግንቦት የክህነት ስልጣን መሪዎች በሚስዮን የሚያገለግሉ ባልና ሚስት የመኖሪያ ወጪከተመደበውበላይ ከሆነ የቤተክርስቲያኗ የሚስዮን ድርጅት ለመክፈል እንደሚችል ማስታወቂያ ተሰጥቷቸዋል። ይህ ምን አይነት በረከት ነው! በሚስዮን ለሚያገለግሉ ባልና ሚስት ይህ ወጪከኑም በላይ ታላቅ የሆነ ውነ ው። ወንድሞችም በሚስዮን የሚያገለግሉ ባልና ሚስት ለ 6 ወር ወይም አመት እና ከ 18 ወር እስከ 24 ወር ለማገልገል እንደሚችሉም ወስነዋል። በአስደናቂ ማበረታቻም፣ ለአስፈላጊ የቤተሰብ ጉዳይ በሚስዮን የሚያገለግሉ ባልና ሚስት ወደቤት ለመመለስ ይችላሉ። እንደ 19 አመት ወጣቶች በር በበር እያንኳኳን መሄድ አለብን ብላችሁ አትጨነቁ። ይህን እንድታደርጉ አንጠይቃችሁም፣ ነገር ግን ልታደርጉት የምትችሉት ብዙ ነገሮች አሉ።

ወንድሞች፣ በጤንነት፣ በቤተሰብ፣ ወይም በገንዘብ ምክንያት አሁንም ይሆን በምንም ለምስዮን ለመሄድ አንዳንዶቻችሁ እንደማትችሉ እናውቃለን። ነገር ግን አላማ በማድረግ ብዙዎቻችሁ ለመሄድ ትችላላችሁ።

ኤጲስ ቆጶሶችና የካስማ ፕሬዘደንቶች፣ በሸንጎአችሁና በጉባኤአችሁ እነዚህን ተነጋገሩበት። በስብሰባችሁ ተቀምጣችሁ እና በጸሎት የትኞዎቹ ጥሪ ለመቀበል እንደሚገባቸውስሜታ እንዲኖራችሁ የተሰበሰቡትን ተመልከቱ። ከእዚያም ከእነርሱ ጋር ተገናኙና ለአገልግሎት ቀን ወስኑ። ወንድሞች፣ ይህ ሲሆን፣ ባለቢታችሁን የቲቪ መቆጣጠሪያውንና ሶፋችሁን ትታችሁ ለመሄድ ከቻላችሁ፣ እነርሱ ከልጅ ልጆች ለመለየት እንደሚችሉ ንገሯቸው። ትትንሾቹ ደህና ይሆናሉ፣ እናም ጌታን በማገልገል ልታድርጉላቸውየ ምትችሉት በቤት ቆይታችሁ ስትንከባከቧቸውከምታደርጉት በላይ እንደሚሆን ቃል እገባላችኋለሁ። “በዚህ ቤተሰብ ውስጥ እኛ በሚስዮን እናገለግላለን!” ከሚል በላይ ምን አይነት ታላቅ ስጦታ ለትውልዳችሁ ለመስጠት ትችላላችሁ።

በዚህች ትልቅ እና አስደናቂ ቤተክርስቲያን ውስጥ ማድረግ የሚገባን የሚስዮን ስራ ብቻ አይደለም። ነገር ግን ልናደርጋቸውየሚያስፈልገን ነገሮች ሁሉ የሚመኩት መጀመሪያ ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን እና ወደ እምነቱ ስለመምጣት በመስማታቸውላይ ነው። ለዚህምነውኢየሱስ ለደቀመዛመርቱ የሰጠውየመጨረሻ ሀላፊነት “እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው” የሆነ ው። ከእዚያም የሚሩት የወንጌል በረከቶች፣ እንዲሁም የቤተሰብ አንድነት፣ የወጣቶች ፕሮግራም፣ የክህነት ስልጣን ቃል ኪዳን፣ እና ወደ ቤተመቅደስ ድረስ የሚፈሱት ስነስርዓቶች ይከተላሉ። ነገር ግን ኔፊ እንደመሰከረው፣ “በበሩ እስከሚገቡ ድረስ” ማንም ሊመጣ አይችልም። ወደ ዘለአለም ህይወት በሚመራውመነገድ ላይ መደረግ ካለባቸው ሁሉ፣ ያን በር የሚከፍቱ እና ሌሎችን በዚህ እንዲገቡ የሚረዱ ብዙ ሚስዮኖች ያስፈልገናል።

የክህነት ባለስልጣን ለሆነውእያንዳንዱ ሰው፣ ጠንካራ እና መለኮታዊ ለሆነ ድምፅ፣ ከክፉ ጋር እናም የክፋት ምሳሌ ከሆነውጋር ለሚዋጋ ድምፅ ብቻ ሳይሆን፣ ለመልካም

የሚሆን ድምፅ፣ የወንጌል ድምፅ፣ ፤ዕግዚአብሔር ድምፅ ጥሪ አቀርባለሁ። እድሜችሁም ምንም የሆነ ውወድሞች፣ አንደበታችሁን አስፈቱ እናም “የት ለማግኘት እንደሚችሉ ስለማያውቁ ከእውነቱ ለተደበቁባቸው” ቃላቶቻችሁ ታዕምራት ሲሰሩ ተመልከቱ።

ወደ ጦርነቱ በፍጥነት ሂዱ፣ ወደ ሜዳው በቶሎ፤
እውነት ኮባችን፣ ቀበቷችን፣ እና ጋሻችን ነውና።
በአርማችሁ ቁሙ፣ በኩራት ይውለበለባሉ!
በደስታ፣ በደስታ፣ ወደቤታችን እንሰለፋለን።

በመምህራችን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ አሜን።